ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት Debre markos University newsletter

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ዜና መጽሄት

# Debre Markos University Newsletter

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በየወሩ የሚታተም

Monthly Newsletter Published by the Corporate Communications Directorate

ቅጽ-3 ቁጥር-20 የህዳር ወር 2007 ዓ.ም እትም Volume-3 Number-20 Nov 2014 G.C Release

የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን በዓል ማክበር ዩኒቨርሲቲዎች የትንሿ ኢትዮጵያ መገኛ በመሆናቸው ተማሪዎች በማንነታቸው እንዲኮሩ፣ ተግባብተውና ተቻችለው እንዲኖሩና አንዱ የሌላውን ባህል እንዲያውቅ ያስችላል ---------------------------------------- 2

ስለእግር እብጠት በሽታ እያደረገ ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም፣ በጮቄ ተፋሰስ ልማትና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ---------------------------- 4

የሁሉም ኮሌጆች የነባር ተማሪዎችና የመምህራን የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች ክለሳ ተደርጎ ወደ ስራ ተገብቷል --------------------------- 5

የልምድ ልውውጥ በማድረግ የሚሰሩ ስራዎችን በትምህርት፣ በጤናና በተጠቃሚነት ዙሪያ ወጣቶችና ሴቶች የተፈጠረላቸውን የስራ እድል መነሻና መድረሻ ተሞክሮ ወስዶ ተግባራዊ ለማድረግ ------------------------------------------- 8

## በውስጥ ገፆቻችን

የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በደማቅ ሁኔታ ተከበረ -------------------------------- 2

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተቋማዊ ብቻ ሳይሆን አገራዊ ራዕይ ሰንቆ እየሰራ መሆኑ ተገለፀ ------------------------------------------------- 4

የጥቅምት ወር የለውጥ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ሪፖርት ለአመራ ፎረሙ ቀርቦ ውይይት ተደረገበት ---------------------------------- 5

የአዲስ አበባ አማራ ሴቶች ማህበር አባላት ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በመገኘት ጉብኝት አደረጉ ------------------------------------------------- 7

Debre Markos University celebrates nations, nationalities & peoples day colorfully -------- 10

Debre Markos University Top and Middle Level Officials make educational visit to Jimma & Wollega Universities ----------------- 11

Addis Ababa, Amhara Females' Association Members Visit Debre Markos University ----------------------- 12



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# ራዕይ

# Vision

## እ.ኤ.አ. በ2030 ከዓለም ካሉ ታዋቂ ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ሆኖ መገኘት፡፡

Debre Markos University aspires to be world class University in 2030.

# ተልዕኮ

# Mission

## ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትና ስልጠና በመስጠት ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ማፍራት

Producing competent and innovative professionals through providing quality instructional, CoCurricular and cultural involvement.

## አጋር አካላትን በማሳተፍ ችግር ፈች ጥናትና ምርምር ማድረግ፣

Carrying out problem solving research through the active involvement of stakeholders and,

## ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የማማከርና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለሃገራችን ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ፣

Providing demand driven community and consultancy services.



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዓል በደማቅ ሁኔታ ተከበረ

በሁሉንአየን ጋሻው

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ 9ኛው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ቀን በዓል በተለያዩ ዝግጅቶች በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ከህዳር 27-29/2007 ዓ.ም. በተለያዩ ዝግጅቶች በደማቅ ሁኔታ አከበረ፡፡



የኪነ-ጥበብ ሥራዎች በቀረቡበት ወቅት

የዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ምክትል ዳይሬክተር፣ አቶ አብዩት አንማው በደብረ ማርቆስ ከተማ ንጉስ ተክለሃይማኖት አደባባይ የተዘጋጀውን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል አከባበር በንግግር ሲከፍቱ እንደገለፁት ሀገራችን ለረዥም ዘመናት በፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ ስትማቅቅ የነበረችና ዜጎች መብታቸውንና ጥቅማቸውን በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ ማስጠበቅ የሚችሉበት ዕድል እንዳልነበረ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም የጀመርነውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመጠቀም የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ በህብረ-ብሔራዊነታችን ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግና ተገቢውን የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለአገራችን የህዳሴ ጉዞ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ማበርከት እንደሚጠበቅበት ጠቁመዋል፡፡

በዩኒቨርሲቲያችን የሚገኙ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችም የተጀመረውን የህዳሴ ጉዞ የበለጠ ለማፋጠንና ከልማቱ ተጠቃሚ ለመሆን በወንድማማችነት፣ በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተውን አንድነታችንን የምናጠናክርበት ጊዜ መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባ አክለው ገልፀዋል፡፡

የደብር ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ህብረት ህዝብ ግንኙነት ተጠሪ የሆነው ተማሪ አዳፍር ታደሰ በበኩሉ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን በዓል ማክበር ዩኒቨርሲቲዎች የትንሿ ኢትዮጵያ መገኛ በመሆናቸው ተማሪዎች በማንነታቸው እንዲኮሩ፣ ተግባብተውና ተቻችለው እንዲኖሩና አንዱ

የሌላውን ባህል እንዲያውቅ ያስችላል ብሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በአንድነት ለነገዋ ኢትዮጵያና ለመጭው ትውልድ የተሻለ ለመስራት ያስችላል፡፡ በአጠቃላይም አብሮ የመኖር ባህልን፣ አንድነትን፣ ፍቅርንና ቀና አስተሳሰብን ለማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ገልጿል፡፡

ዩኒቨርሲቲው የብሔር፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን በዓል በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢና ውጭ በተለያዩ ዝግጅቶች የተለያዩ የደብረ ማርቆስ ከተማ ማህበረሰብና የዩኒቨርሲቲው አመራሮች፣ መምህራንና ተማሪዎች በተገኙበት አካሂዷል፡፡ በበዓሉ አከባበር የጥያቄና መልስ ውድድር፣ የኪነ-ጥበብ ስራዎች (ግጥም፣ መነባንብና ድራማ) እንዲሁም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ከሚገልፁና ከሚያሳዩ ጣዕመ ዜማዎች ጋር ቀርበዋል፡፡

በሌላ በኩል በዩኒቨርሲቲው የተማሪዎች ህብረት፣ የሀዲስ አለማየሁ የባህል ተቋም፣ የሰላም ፎረምና የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት አስተባባሪነትና የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ፣ የደብረ ማርቆስ ከተማ ነዋሪዎችና የተለያዩ አመራሮች የታደሙበት የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አለባበስና ባህል ዝግጅት በደብረ ማርቆስ ከተማ ንጉስ ተክለሃይማኖት አደባባይ ተካሂዷል፡፡ በዝግጅቱ የሁሉም ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አለባበስና ባህል ለታዳሚዎች ትውውቅ ተደርጓል፡፡



የብሔር ብሔረሰቦች ከፊል ገጽታ

በተጨማሪም ሁሉንም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያሳተፈ የሸክላ ሰበራ ውድድር በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ የተካሄደ ሲሆን በፕሮግራሙ ላይ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የተለያዩ ሙዚቃዎች በባንድ ታጅበው ቀርበዋል፡፡ በመጨረሻም ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ተከባብረውና ተቻችለው እየሰሩበት እንደሚገኙ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

# ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተቋማዊ ብቻ ሳይሆን አገራዊ ራዕይ ሰንቆ እየሰራ መሆኑ ተገለፀ

በሁሉንአየን ጋሻው

ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በድሬዳዋ ከተማ አዘጋጅነት በተካሄደው 6ኛው የከተሞች ሳምንት በመማር ማስተማሩ፣ በምርምሩና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፎች እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ የሚያሳይ የፎቶ አውደርዕይ ለታዳሚዎች አቀረበ፡፡



የአውደ ርዕዩ ከፊል ገጽታ

ዩኒቨርሲቲው በኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት አከባበር ላይ የዩኒቨርሲቲውን አመሠራረት፣ የትምህርት ክፍሎችንና ኮሌጆችን ዕድገት፣ አጠቃላይ የሰው ሃይል መረጃ፣ መማር ማስተማር እንቅስቃሴ፣ የጥናትና ምርምር ስራዎች፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጮቄ ተፋሰስ ስራዎች የትብብርና አጋርነት ስራዎች፣ የቢዝነስ ስራዎች፣ የለውጥ ፕሮግራሞች አፈፃፀም፣ የስርዓተ ፆታ፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስና አካል ጉዳተኞች ጉዳይ እንቅስቃሴዎች፣ የተማሪዎች እንቅስቃሴ እንዲሁም ሌሎች በዩኒቨርሲቲው እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትና የመጡ ለውጦች ለታዳሚዎች በኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ገለፃ ተደርጐላቸዋል፡፡

የከተሞች ሳምንት በዓል አከባበር ታዳሚ የነበሩ ግለሰቦች እንደገለፁትም ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከሌሎች የውጭ ሃገራት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በአለው የትብብርና አጋርነት ሥራውና የሚያደርገው የልምድ ልውውጥ ወደ ተሻለ ደረጃ እንደሚያራምደው ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ዩኒቨርሲቲው እያደረገ ያለው የምርምር እንቅስቃሴ የክልሉን ዕድገት የሚያፋጥንና ለሌሎች ተቋማት አርአያ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተጠቁሟል፡፡ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍም የአካባቢው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር በሆነው በእግር እብጠት በሽታ ላይ እያደረገ ያለው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ፣ በጮቄ ተፋሰስና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን ከሻሸመኔ የመጡት ታዳሚ አቶ ጌታነህ ንጉሴ ገልፀዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

በአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲው በመማር ማስተማሩ፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራቶችን ውጤታማ ለማድረግ ለገቢ ማመንጫነት ያቋቋመው የመንቆረር አግሮ ኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዝ እንቅስቃሴ ገንዘብ ከማመንጨት አልፎ የምርምር ሥራዎች እየተሰሩበት ያለ መሆኑ በጣም የሚደነቅ ተግባር ነው ተብሏል፡፡

በመጨረሻም ዩኒቨርሲቲው እየሰራ ያለው ስራ ተቋማዊ ብቻ ሳይሆን አገራዊ በመሆኑ የተጀመሩት እንቅስቃሴዎችን አጠናክሮ በመቀጠል የዩኒቨርሲቲውን ራዕይና ተልዕኮዎች ማሳካት እንደሚቻል የዝግጅቱ ተሳታፊዎች እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡ የከተሞች ሳምንት በየዓመቱ ከተሞች ያሏቸውን እንቅስቃሴዎችንና ለውጦችን የሚያሳዩበትና የሚያስተዋውቁበት ዝግጅት መሆኑ ይታወሳል፡፡

## የጥቅምት ወር የለውጥ ፕሮግራሞች አፈፃፀም ሪፖርት ለአመራ ፎረሙ ቀርቦ ውይይት ተደረገበት

በሰሎሞን አበበ

በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የሁሉም ኮሌጆች፣ የህግ ትምህርት ቤትና የቡሬ ካምፓስ የጥቅምት ወር የለውጥ ስራዎች አፈፃፀም በተቋማዊ ለውጥ ጽህፈት ቤት ተደራጅቶና ለአመራር ፎረሙ ቀርቦ ውይይት ተደረገበት፡፡



ዶ/ር አበበ አድማሱ የኮሌጆችን የለውጥ ሥራዎች አፈፃፀም ሲያቀርቡ

የዩኒቨርሲቲው የተቋማዊ ለውጥ ጽህፈት ቤት ኃላፊ ዶ/ር አበበ አድማሱ እንዳብራሩት የሁሉም ኮሌጆች የነባር ተማሪዎች እና የመምህራን የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች ክለሳ ተደርጐ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ አዲስ ተማሪዎች በአንድ ለአምስትና በልማት ቡድን እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ በሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ ለ2007 ዓ.ም. የቀረቡ የመምህራን የምርምር ፕሮፖዛሎች በየልማት ቡድናቸው መገምገማቸው፣ ተማሪ አሳታፊ የማስተማር ዘዴን ለማስቀጠል ውይይት መደረጉ፣

በቴክኖሎጂ ኮሌጅ የተመራቂ ተማሪዎች ፕሮጀክት ርዕስ መረጣ በልማት ቡድኖች አማካኝነት መከናወኑ እና የኮሌጁን የሱፐርቪዥን ቡድን በትምህርት ክፍል ደረጃ የማደራጀት ስራ መሰራቱ አበረታች ጅምር መሆኑ ተገልጿል፡፡ በግብርናና ተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ኮሌጅም በእጽዋት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ለሴት ተማሪዎችና ውጤታቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ወንድ ተማሪዎች ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግ ኮሚቴ መቋቋሙ፣ እንስሳት ሳይንስ ትምህርት ክፍል በ2006 ዓ.ም. የተሻለ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች እውቅና መስጠቱ፣ በአንድ ለአምስት አደረጃጀት የአመለካከት ክፍተት ላለባቸው ተማሪዎች እና ለአዲስ ተማሪዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መስራቱ፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ ትምህርት ክፍል ለሴት ተማሪዎች የቱቶሪያል ድጋፍ መስጠት መጀመሩ እና የትምህርት ክፍሉ ሱፐርቪዥን ቡድን የመማር ማስተማር ሂደቱንና የከታታይ ምዘና አፈፃፀሙን የመገምገም ሥራ መከናወኑ ተጠቃሽ መሆናቸው ተጠቁሟል፡፡

በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ በኩል ለተማሪ አደረጃጀቶች አማካሪ መምህራን መመደባቸውና በኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች በአደረጃጀታቸው የተባዙ መጽሐፍትን እንዲያነቡ መደረጉ ተጠቁሟል፡፡ በህግ ትምህርት ቤት መምህራን የልማት ቡድኖች መካከል ደረጃ መስጠቱ እንዲሁም በህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ከሁሉም የመምህራን የአንድ ለአምስት ቡድኖች የተውጣጡ መምህራን የስርዓተ ትምህርት ክለሳ ማደረጋቸው ተገልጿል፡፡

እንደ ዶ/ር አበበ ገለፃ በቢ.ኤስ.ሲ መሰረት መምህራንና ሰራተኞች ከቅርብ ተጠሪያቸው ጋር በውጤት ተኮር የምዘና ስርዓት የስራ ውል መያዣ ቅጽ መሰረት ውል መያዛቸው፣ የካይዘን ትግበራንም በተመለከተ አዲስ የተመደቡትን ቢሮዎች ለስራ ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ የፕላስቲክ ምንጣፍ እንዲነጠፍላቸው መደረጉ፣ በቢሮዎችና በመማሪያ ክፍሎች የማስታወቂያ ቦርዶች ተዘጋጅተው አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ስራ መከናወኑን ተናግረዋል፡፡

የለውጥ ፕሮግራሞች አፈፃፀም በቀረበበት ሰዓት የህዝብ ክንፍን የጥቅምት ወር ሪፖርት ያቀረበው የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ህብረት ፕሬዚዳንት ተማሪ ጥላሁን ድረስ እንደገለፀው በአንዳንድ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ያለውን ችግር በመጥቀስ መፍትሔ እንዲፈለግላቸው አመልክቷል፡፡ እንደተማሪ ጥላሁን ማብራሪያ የመማር ማስተማር ሒደቱ ጥሩ ሒደት ላይ ቢሆንም እስካሁን መምህራን ያልተመደቡባቸው ኮርሶች እንዳሉ በመግለጽ አስቸኳይ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ጠይቋል፡፡

በመጨረሻም የደብረ ማርቆስስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ጥላዬ ጌቴ በማጠቃለያ ሃሳባቸው እንዳስቀመጡት በቁልፍ ተግባር አፈፃፀም በሁሉም ዘርፎች ወቅታዊ ሥራዎች በቼክ ሊስት መውረዱ፣



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

ከነችግሩም ቢሆን በሁሉም ኮሌጆች ወርሀዊ የአፈፃፀም ሪፖርት ተቋማዊ ለውጥ ጽህፈት ቤት መላኩና በተማሪዎች ህብረት በኩል የትምህርት ልማት ሰራዊት አደረጃጀት ስርዓት ዘርግቶ ክትትል መደረጉ እና ያልተጀመሩ ኮርሶችን ለይቶ ማቅረብ መቻሉ በጥንካሬ የሚታይ አፈፃፀም ነበር ብለዋል፡፡ እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለፃ የልማት ቡድን አደረጃጀቱ በተማሪዎች ላይ ብቻ ማተኮርና የመምህራኑን አደረጃጀት በተሟላ መልክ አለመፈም፣ የሱፐርቪዥን ቡድኑን በሁሉም ደረጃ አጠናክሮ ድጋፍ አለመስጠት፣ ሁሉም አደረጃጀቶች የተሟላ ወቅታዊና ተገቢ እቅድ አዘጋጅተው አለመንቀሳቀስና ትምህርት ያልተጀመረባቸው ኮርሶች መኖር በእጥረት መስተካከል የሚገባቸው መሆኑን አሳስበዋል፡፡ በውጤት ተኮር ምዘና ስርዓት ውል መያዙና ወደ ተግባር መገባቱ፣ አዳዲስ ቢሮዎችን አቅም በፈቀደ መጠን ለማደራጀት መሞከሩ፣ ሁሉም ኮሌጆች ነባር አደረጃጀቶችን መከለሳቸውና አዲስ ተማሪዎችን ለማደራጀት ጥረት መደረጉ በለውጥ መሣሪያዎች አፈፃፀም የታዩ መሆናቸውን ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል፡፡

## የአዲስ አበባ አማራ ሴቶች ማህበር አባላት በደብረ ደርቆስ ዩኒቨርሲቲ ጉብኝት አደረጉ

በሰሎሞን አበበ

የአዲስ አበባ አማራ ሴቶች ማህበር አባላት "በተደራጀ የሴቶች ተሳትፎ ህዳሴያችን ይሳካል!" በሚል መሪ ቃል በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በመገኘት የስራ ጉብኝት አደረጉ፡፡



የአዲስ አበባ የአማራ ሴቶች ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲን ሲጎበኙ



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

የአዲስ አበባ አማራ ሴቶች ማህበር ሥራ አስፈፃሚ ወ/ሮ ፀሐይ ከበደ እንዳብራሩት የዚህ ጉብኝት ዋና ዓላማ በክልላችን የሚሰሩ ስራዎች ምን ይመስላሉ የሚለውን በማየት ተሞክሮ የሚሆኑ ልምዶችን ይዞ በመሄድ አዲስ አበባ ላሉ የአማራ ሴቶች ልማት በምን ደረጃ እንዳለ ለማሳየትና የሴቶች ልማት ቡድን አደረጃጀት አሰራር ምን ይመስላል የሚለውን በመውሰድ ምን ልንተገብር እንችላለን የሚለውን ለመረዳት ነው፡፡ እንደ እርሳቸው ገለጻ ሌላው የልምድ ልውውጥ በማድረግ የሚሰሩ ስራዎችን በትምህርት፣ በጤናና በተጠቃሚነት ዙሪያ ወጣቶችና ሴቶች የተፈጠረላቸውን የስራ እድል መነሻና መድረሻ ተሞክሮ ወስዶ ተግባራዊ ለማድረግ ነው፡፡

የአዲስ አበባ አማራ ሴቶች ማህበር አባላት የዩኒቨርሲቲውን የወተት ሀብት ልማትና የስጋ ከብቶች ማድለቢያ ጣቢያ በጎበኙበት ሰዓት ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ምስጋናው ጋሻው እንደገለፁት ዩኒቨርሲቲው ከመማር ማስተማር፣ ከጥናትና ምርምር እንዲሁም ማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች በተጨማሪ፣ ዩኒቨርሲቲው በሀገራችን ያለውን የበጀት እጥረት ለመቅረፍ ገቢ ሊያስገኙ የሚችሉ ስራዎች ላይ ተሰማርቶ ይገኛል፡፡

በዚህም ምክንያት መንቆረር አግሮ ኢንዱስትሪ ኢንተርፕራይዝ የሚባል ድርጅት አቋቁሞ በእንስሳት ልማት፣ በወተት ምርትና ከብት ማድለብ እንዲሁም በሰብል ምርት ከ1080 ሄክታር መሬት በላይ በኢንቨስትመንት ተቀብሎ ልዩ ልዩ አዝርእቶችን እያመረተ ይገኛል፡፡ በሀገራችን ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለየት የሚያደርገው ቢዝነስ ስራዎች ላይ ተሰማርቶ መገኘቱ ነው ብለው ዳይሬክተሩ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

የመንቆረር አግሮ ኢንዱስትሪ የእንስሳት ባለሙያ አቶ በቃሉ በበኩላቸው የወተት ልማት ጣቢያው ቁጥራቸው 23 የሚሆኑ የወተት ላሞች በማስመጣት የወተት እርባታ ስራው እየተከናወነ መገኘቱን ገልጸዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓትም 25 ጥጆች ተወልደው በጠቅላላው 48 የወተት ላሞች ሆነዋል፡፡ በቀን ከ175 እስከ 200 ሊትር ወተት እየተመረተ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ እያቀረበ እንደሚገኝም አቶ በቃሉ አያይዘው አብራርተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእንስሳት ሳይንስ ትምህርት ክፍል ተማሪዎችም የተግባር ትምህርት እንዲያገኙ እየተደረገ ነው በማለት ገልፀዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication



የደ/ማ/ዩ የወተት ላሞችን እርባታ ጣቢያ ሲጎበኙ

በመጨረሻም የአዲስ አበባ የአማራ ሴቶች ማህበር አባላት በኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀውን የዩኒቨርሲቲው ማስተዋወቂያ የፎቶ አውደ ርዕይ ጎብኝተዋል፡፡ በአውደ ርዕይ ጉብኝታቸው ላይም ዩኒቨርሲቲው አመሰራረት፣ የመምህራንና ሰራተኞች ቁጥር እድገት፣ በመማር ማስተማር ያሉትን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች፣ በማህበረሰብ አገልግሎት የተከናወኑ ተግባራትና በምርምር ረገድ የተሰሩ ሥራዎች ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ገላጭ ፎቶ ግራፎችን በአውደ ርዕዩ ወቅት ጎብኝተዋል፡፡



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 ✉ 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication

# Debre Markos University Celebrates Nations, Nationalities and Peoples Day Colorfully

Debre Markos University celebrates the 9th Ethiopian Nations, Nationalities and Peoples day colorfully through various activities in and out side the compound from January6-8 2014 for three concequtive days.



**Artistic performances**

Mr. Abyot Animaw, Debre Markos University students Service Directorate Deputy Director, opening the nations, nationalities and peoples day celebration program held in Debre Markos town, Nigus Tekile Haimanot square, states that Ethiopia has been in anti-democracy regime for a long period of time. Citizens could not assure their rights and benefits in peaceful and legal grounds, he added. Thereby, conducting researches on the diversity of nations and nationalities and providing appropriate community services to put their finger prints in the movement of the country towards renaissance should be the responsibility of Debre Markos University community, Abyot recommended. Thus, celebrating nations, nationalities and peoples day in the University could enable students to strengthen brotherhood, tolerance and know their culture one another.

Student Adafer Tadese, Debre Markos University Students Union Public Relation delegate, on his part explains that celebrating nations, nationalities and peoples day enables students to be proud of their cultures, tolerate one another and share their cultures as Universities are the place where nations, nationalities and peoples are available. In addition to this, it would enable nations, nationalities and peoples to work

together for the tomorrow of the country and the coming generations. Generally, it has pivotal roles to develop a culture of tolerance, unity, love and good thinking, he added.

The university celebrates nations, nationalities and peoples day in various programs in and outside the compound with the presence of dwellers of Debre Markos town, leaders of the university, instructors, administrative staffs and students

In the celebration, artistic performances (poem, recitation and drama) including question and answer competition are performed in the presence of Debre Markos University community. Nations, nationalities and peoples cultural dressings accompanied by their respective songs presented to the participants on the stage.

In addition to this, nations, nationalities and peoples cultural dressings and customs show presented by the students on Debre Markos Nigus Teklehaimanot Square in the presence of the community of the town, leaders of the university and students which was prepared and organized Corporate Communication Directorate in collaboration with Haddis Alemayehu Cultural Studies Institute, Students union and Peace forum.

Finally, it is noted that nations, nationalities and peoples are working with peace and tolerance in Debre Markos University.

## Debre Markos University Top and Middle Level Officials make educational visit to Jimma and Wollega Universities.

Debre Markos University Top and Middle Level Officials make educational visit to Jimma and Wollega Universities from December 1 to 7, 2014. Expressing the objective of the trip, Debre Markos University President Dr. Tilaye Getie conveyed that the trip is one of the scheduled activities for the academic year. As these universities have registered nationally recognized and meaningful developments, experience drawn from these universities will be righteous inputs for the Debre Markos University's endeavour in excelling teaching learning, research and community service, the president added.



**DMU Delegates**

Accordingly best and fitting experiences will be counted in Debre Markos University's Second Growth and Transformation Plan (2008-2013 E.C). It is noted that each delegates of the University has took excellent experiences from their respective departments in Jimma and Wollega Universities. It's praised that developed community service, staff's commitment and impeccability, and ICT development are some of the notable qualities of these universities. Finally, participants of the educational visit express their deepest acclamation for the excellent cordiality and openness of the hosting universities.

## Addis Ababa, Amhara Females' Association Members Visit Debre Markos University

Addis Ababa, Amhara Females' Association Members visit Debre Markos University under the theme "We can achieve our Renaissance through organized females' participation".

W/zero Tsehay Kebede, Addis Ababa, Amhara Females Association leader states that the objective of the tour is to see the activities in the region and to formulate best experiences to share to females in Addis about their regional development and able to



0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64 269 E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication



see females organization to identify areas of support. In addition to this, it is to see the activities done in education and health that could benefit youths & females in creating job opportunity and the changes made as they can be models and make them practical.

**Partial view of the visit**

Ato Misganaw Gashaw, Debre Markos University corporate communication Directorate Director, on the opening floor of the visit in dairy production and fattening activities of the university states that the university is working in income generating activities besides to the core activities teaching learning, research and community services. As to his explanation as there is a deficit in budget allocation, the university is working in income generating activities planning to cover 25% of its annual budget by the enterprise. Thus, the university established Menkorer Agro Industry Enterprise. The Enterprise is working in animals production in dairy products, fattening cattle, and crops production by taking 1080 hectares of land from Baso Liben Woreda Wontu Kebele and Machakile Woreda Yewla kebele.



Visitors in the dairy production stall

Ato Bekalu Yitayew, Menkorer Agro Industry Enterprise Animals professional on his part says that dairy production activity was started by 23 female calves bought from Haramaya University and their numbers increases to 48 having 25. Newly born calves from the earlier ones. . Now a days they are giving 175-200 liters of milk per day and these is being sold to the community in a minimum price. Besides to this, animal science students are taking practical trainings and conducting researches in the enterprise.

Finally, Addis Ababa Amhara Females" association Members express that they could have a clear understanding about the university through a photo symposium made by Corporate Communication Directorate including brief explanation about its establishment, development of staffs, activities done in the teaching-learning, research and community service wings Moreover, They express their happiness over the activities they watched in the university as there is improvement and development. They also suggest that the university has to strengthen its support to the female students, teachers and administrative workers so as to bring them to leader position.



**0913-14-96-80 Fax. 058-771-17-64** **269** E-mail: dmu.edu.et@gmail.com Website: www.dmu.edu.et Facebook: dmu comunication